# የመለስ አምልኮን በጨረፍታ "የቁጭትና የህዳሴ ትውልድ"

**(ክፍል አምስት)**

ዮናስ 7/30/12

*የፍትሕ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በሆነው አቶ ተመስገን ደሳለኝ የቀረቡ መጣጥፎች ጥርቅም ስለሆነውና "የመለስ አምልኮ "በሚል በወጣው መጽሃፍ ላይ ተመስርቼ ከዚህ ቀደም ለንባብ በበቁት አራት ጨረፍታዎች በአቶ ተመስገንና በፍትሕ ጋዜጣ ዙሪያ ስለተሰባሰቡት አምደኞች ማንነትና ፍላጎት በግልጽ ተነጋግረናል። የመለስ አምልኮ አምሰተኛውና የመጨረሻ ክፍል ውስጥ የተዳሰሱ ነጥቦችን ደግሞ በዛሬው ጨረፍታዬ የምናያቸው ይሆናሉ።*

*የፖለቲካ ጫወታ ላይ ናቸው ስንል የምሽግ ወጊያ ውስጥ ይገኛሉ፣ ሰላማዊ ትግል እያደረጉ ነው ብለን ከመናገራችን በሽብር እንቅስቃሴ ውስጥ ዋነኛ አበረታች በል ሲልም ተዋናይ ሆነው ይታያሉ፤ ለዴሞክራሲያዊ የምርጫ ስርዓት ተገዢዎች ናቸው ብለን ከመገመታችን ከምርጫ አስቀድመው ውጤቱን በራሳቸው ወስነው ምርጫው ስለሚጭበረበር መካሄድ የለበትም፤እኛ የለንበትም፤አልፎ ተርፎም ምርጫ ቦርዱ መፍረስ አለበት ይላሉ፡፡ ሰከኑ የሚለውን ዜና ሰምተን ሳንጨርስ ይግላሉ፤ ለህዝባችን ብለው የፈረሙት ሳይደርቅ ለእኔ እና የእኔ በሚል ተቧቀሱ የሚል ዜና እናነባለን፤ እየገነባን ነው እያሉ ከስር መሰረቱን ይንዳሉ፤ ምለው ሳይጨርሱ ቃላባይ ይሆናሉ።*

*ሳይጀምሩ ይጨርሳሉ፤ ጭራ የሌላቸው የማይያዙና የማይጨበጡ ፣ብቻ በጥቅሉ ከእስስትም በላይ የሆነ ባህሪ አላቸው፤ የዜሮ ድምር ፖለቲከኞች። ከፀጥታ ይልቅ ትርምስን፣ ለአጀንዳቸው ማስፈፀሚያ ሲሉ ይመርጣሉ፤ ጋዜጠኛ ነኝ ይሉና የፖለቲካ መድረክ ይመራሉ፤ ፖለቲከኛ ነኝ ይሉና ጋዜጠኛ ሆነው ሪፖረት ይሰበስባሉ፤ ከትርምስ ለማትረፍ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለም በጨረፍታዎቼ ተመልክታል።*

*5ተኛውና የመጨረሻው ክፍል የመለስ አምልኮ መጣጥፎች ደግሞ ማሳረጊያ በመሆናቸው ነው መሰል፤ የትርምስ እና የጩኸት ደረጃቸው ከፍ ያለ፤ የአመጽና የብጥብጥ ትርክታቸው ጫፍ የነካ፤ የሚሹት ሁሉ ባለመሳካቱ ቁጭታቸው ገኖ የሚታይበት፤ ደግሞ እንጥፍጣፊ እድሎችን ለመጠቀም*

ሙከራ የሚደረግበት በአጠቃላይ ከጩኸት ጋር ውል የተሳሰሩ መሆናቸውን የምናረጋግጥባቸው መጣጥፎች ናቸው።

|ህዝባዊ ብሶቶች´ ይላል የክፍሉ አቢይ ርዕስ፤ ወደ መጀመሪያው ርዕሰ ጉዳይ ስንሻገር ደግሞ |ኢትዮጵያኒዝም´ ወደ |ቱኒዚያኒዝም´ ያልተቋጨ የአብዮቶች ዋዜማ´ የሚለውን እናገኛለን። በዚህ ርዕሰ ጉዳይ የተነሳውና የመጣጥፉ ግብ የቱኒዚያና የግብጽ አብዮች በኢትዮጵያ ባለመደገሙ ተመስገንና ስብስቡ መቆጨቱንና አሁንም አረፈደምና  መደገም አለበት የሚል የሞኝ መልእክት ነው።

ይቀጥላል፦ |የፀጥታ ጩኸት´ ይህም ቢሆን ከሌሎቹ መጣጥፎች የተለየ አይደለም። መነሻና መድረሻው አመጽ ነው። ይዘቱ በጩኸት የታጀለ ነው። ለመቀስቀሻነት የሰፈሩት ደግሞ በመንግስት በኩል መፍትሂ የተበጀላቸውና በመሻሻል ላይ የሚገኙ ያለፈባቸው አጀንዳዎች ናቸው። የኑሮ ውድነቱ ህዝቡን ሰንጎ ይዞታል፤ የስራ አጥነት ወጣቱን አስቆዝሞ ግራ አጋብቶታል፤ የቤት ችግር ደግሞ ብሶቱን ጫፍ አስነክቶታል ፤ነጋዴውም ቢሆን ያለምትክ ሱቁ እየተወረሰ ነው። ስለሆነም የዝምታው ጩኸት በጠርሙሱ አፍ ላይ ደርሷል አይነት ይዘት ያለው ይህ መጣጥፍ ያልራበውን አስርቦ ፣ጤነኛውን አሳምሞ አትራፊውን አክስሮ ላም ባልዋለበት የተደረገ የኩበት ለቀማ ጥሪ ነው።

እንግዲያውማ የኑሮ ውድነቱ ሰበብ ማነው? ብለን ስንጠይቅ ምላሹ ተመስገን በኑሮ ውድነቱ በንግድ ስርዓቱ እየተበሳጩ ነው የሚላቸው ኪራይ ሰብሳቢ ነጋዴዎችና የነሱ ጥገኛ የሆኑ ግለሰቦች ሆነው እናገኛቸዋለን። ሆኖም ግን መንግስት እንደመንግስት የተጣለበትን ሃለፊነት በማረጋጋት ሂደት ውስጥ ገብቶ እየተወጣ ነው። የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በማቋቋም ህዝቡን ከአልጠግብ ባይ ኪራይ ሰብሳቢዎች ከመጠበቅ ባሻገር በህብረት ስራ ማህበራት እና በኢትፍሩት በኩል መሰረታዊ የሆኑ  የፍጆታ ሸቀጦችን በማከፋፈል ላይ መሆኑ በተጨባጭ እና በመሬት ላይ ያለ እውነት ነው።

የቤት ችግርን ለማስወገድ በየትኛውም የኢትዮጵያ  ስርዓተ መንግስት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የጋራ መኖሪያ ቤት(Condominnium) በመገንባትና የ40/60 ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። ስለእውነት ለመናገር ካስፈለገ አዲስ አበባ በ125 ዓመት ታሪኳ ያልሆነችውን እየሆነችና እየታደሰች ነው።  ይቆዝማል የተባለው ወጣት በቁዘማ ላይ ሳይሆን ተደራጅቶ እየሰራ ነው። ቀደም ያሉትማ ከጥቃቀን አልፈው መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን እየገነቡና ለሌሎች ወገኖቻቸው የስራ እድል እየፈጠሩ ነው። በእነዚህ የስራ ሂደቶች ውስጥ ግን ችግር የለም ማለት አይቻልም። በመንግስትም በኩል ስግብግብ አመራሮችና የስራ ኃላፊዎች መኖራቸው የማይታበል ሃቅ ነው። ነገር ግን እነዚህን ስግብግቦች መንግስት እየነቀሰ በማውጣት ላይ የሚገኝ ሲሆን የችግሩ ሰለባ የሚሆነው ህብረተሰቡ እንደተለመደው ዘራፊውን ሁሉ |አመለጠ፣ተወነጨፈ´ ብሎ ከማወደስ ይልቅ ከመንግስት ጋር ተሰልፎ ማኮላሸት የሚጠበቅበት እንደሆነ ሊገነዘብ ይገባዋል።

ችግሮቹ ሁሉ በመንግስትና በመላው ህብረተሰብ የተባበረ ክንድ የሚፈቱ እንጂ እንደተመስገን አባባል በጩኸትና በቁዘማ  የሚያበቁ አይደለም። ተመስገን የሚለው የዝምታ ጩኸት የራሱ ህልምና ምኞት እንጂ የህዝቡ የለት ተለት ኑሮ አይደለም።

|ከሶስት እና ከአራት አመት በፊት በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ የቤተሰቦቻቸውን ፎቶ ዘርግተው የሚለምኑ ብዙዎች ነበሩ። ዛሬ ደግሞ መላ ቤተሰቡን ጎዳና ላይ ይዘው ወጥተው መለመን የጀመሩ እልፍ አእላፍ ሆኑ ለሚመፀወተውም ሆነ እግዚአብሄር ይስጥልኝ ለሚለው የፀጥታ ጩኸቱ ይሰማዋል።ገጽ 227

ይሄ አስተሳሰብ  ከቅንነት የመነጨ ነው? ወይስ ቅንቅንነት ፤ከዚህስ በላይ እንዳሻው የሚለጥፍ |ነፃ ጋዜጠኛ´ ከቶ ከየት ይገኝ ይሆን? ሲጀመር እልፍ አእላፍ ስንት ነው? ቋንቋው የግእዝ ነው። እልፍ አእላፍ ብዙ አስርሺዎች እንደማለት ነው። 100 ሺህ 200 ሺህ ሚሊየንም ከዛም በላይ በእልፍ አእላፍ ውስጥ የሚካተት ነው። ስለሆነም ተመስገን መላውን የአዲስ አበባ ነዋሪ ጎዳና ላይ አውጥቶ መጽዋች በሌለበት ተመጽዋች አድርጎታል።

ምጽዋት ጠያቂ በአዲስ አበባችን የለም እያልኩኝ አይደለም መስሎት ቀዬውን እየጣለ ወደከተማ የተመሙትን ግለሰቦች የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳጉዳይ ሚኒስቴር ጥሩ ስትራቴጂ በመዘርጋት ከሃገሩ ማሳና መሬት ጋር አገናኝቷል። የተቀረውና አድራሻውን በትክክል ማጥራት ያልተቻለውን በሌላ በኩል ደግሞ ወደሃገሩ ቢመለስም የተሻለ አማራጭ የሌለውን ደግሞ መንግስት አደራጅቶ ስራ የፈጠረላቸው ስለመሆኑም ልንክደው የማይቻለን ሃቅ ነው። ቁጥሩ ለሚበዛው ተመጽዋችም ችግሩ በአመዛኙ የአመለካከትና ከጥገኛ አስተሳሰብ ያለመላቀቅ ልማድ ነው። ይህ ጉዳይ እውነት በሆነበት አዲስ አበባ ላይ፤ በታደሰችውና የአፍሪካ መዲናነቷ ይገባታል በሚባልላት መዲና ላይ |እልፍ አእላፍ´ ተመጽዋች በፀጥታ ጩኸት ውስጥ ነው መባሉ ተራ ፕሮፓጋንዳ ነው።

|በርግጥ ግበፃውያን በታህሪር አደባባይ ያሰሙት ጩኸት የፀጥታ አልነበረም። ይልቁንም |ቶሬንዶ´ ከተባለው የአሜሪካኖቹ ዘመናዊ የጦር ጀት ድምጽ አስር እጅ የላቀ ጩኸት ነበር ያሰሙት። ሆኖም ከዚህ ከታህሪር አደባባይ ጩኸት በፊት የፀጥታ ጩኸት ጮኸዋል። የእኛስ የፀጥታ ጩኸት እድሜ ምን ያህል ነው? ስንት አመት ቀረው የቶሬንዶ ጩኸት ለመጮህ? እንጃ!´

የአወልያውንና የመጅሊሱን ጉዳይ ዋልድባና ጉራፈርዳ ሳይቀሩ እንደጥሩ የጩኸት አማራጮች በተመስገን በኩል በአንድ መጣጥፉ ላይ የቀረቡበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። የታህሪርን ጩኸት ለአዲስ አበባ የሚመኘው ተመስገን የማይሆን ምኞት እንደሆነ በፍትህና አምደኞቿን በጨረፍታ መጣጥፎቹ ከተጨባጭ ማሳያዎች ጋር አረጋግጨለት ነበር። ሆኖም የሞኝ ሊቅ የያዘውን አይለቅ ሆኖበት ዛሬም ጮኾ ለማስጮህ እየሰራ ይገኛል። የቶሬንዶን ጩኸት  ለመጮህ ስንት አመት ይቀረናል?

እንጃ ብለህ ለራስህ ጥያቄ መልስ ባትሰጥም እኔ ግን እልሃለሁ፦ አንተ እንደለመደብህ እድሜ ዘላለምህን ትጮህ ካልሆነ በስተቀር የቶሬንዶ ጩኸት ግንቦት 20/1983 ከደርግ ጋር አብሮ ፋይሉ ተዘግቷል።

ወደ |ሹክሹክታው ምንድ ነው? ´ እንሻገር። ይህ መጣጥፍ በይዘትም ሆነ በጭብጥ፤ በዓላማም ሆነ በግብ ቀደም ብሎ ከነበረው |የፀጥታ ጩኸት´ ያልተለየ፣ ህዝቡን ስለአመጽ የሚጎተጉትና በተለየ መልኩ መንግስታዊ ተቋማትን እና መላውን ኢትዮጵያዊ የአመጹ አካል እንደሆነ ለማስመሰል የተሞከረበት መጣጥፍ ነው።

ለነገሩ ጩኸት አምላኪ የሆኑት ተመስገን፣ ፍትህና አምደኞቿ ስለጩኸት ሲሉ ማስረጃ ማገላበጥ አይፈልጉም። ህዝቡን ማንጫጫት ለሚሹ ሃይሎች አስረጅ ማጣቀሻ ማቅረብ ነውር ነው። ለዚህም እኮ ነው ምንም እንኳ |ህገ አራዊት´ ቢሉትም ህገመንግስታችን ስለ መንግስት እና ስለመንግስት ስልጣን ቁልጭ አድርጎ ባስቀመጠበት ሁኔታ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በበሬ ወለደ ትርክታቸው በመቅበር ሹመት ሰጥተው ሲያበቁ ሃገሪቷ ታምሳለች ብለው ያቀረቡት። ለነገሩ እነዚህ ሃይሎች መንግስት ሲያስነጥስ ፈነዳ ማለት ከጀመሩ ከራርመዋልና ሰሚ ጆሮ የላቸውም እንጂ ምኞታቸውማ በዝሆን ታዝላ "ድልድዩን አንጋጋነው አይደል" እንዳለችው ጥንቸል ነው።

አቶ ስዬ አብርሃ የካቲት መጨረሻ 2003 ዓ.ም ላይ ለአዲስ ወሬ ጋዜጣ ህዝቡ ከጓደኛው እና ከአካባቢው ሰው ጋር አንድ ነገር እያንሰላሰለ እንደሆነ <u>ግልጽ ነው የሚል ይዘት ያለው</u> አስተያየት ሰጥተው ነበር። ደግሞም አቶ ስዬ በደፈናው ህዝብ ስላሉ <u>የትኛው ህዝብ</u> እንደሆነም ግራ ገባኝ ።---- የሆነ ሆኖ ግን <u>አቶ ስዬን የመሰለ አንጋፋ ፖለቲከኛ</u> |ህዝቡ እያምሰለሰለ ነው´ ሲሉ ምን ማለት እንደፈለጉ የመተንተኑ ግዴታ <u>የእኛ የጋዜጠኞች</u> በመሆኑ ለመተንተኑ ግብዓት አገኝ እንዳው በሚል ጥቂት ጥረት አደረኩ´ ገጽ 228 ሰረዝ የኔ፤

የተሰመረባቸውን ሃረጋት በጥልቀት እንመልከት፤ የመጣጥፉ መሰረት አዲስ ወሬ ጋዜጣ በመሆኑም አዲስ ወሬ ጋዜጣ ማነው? የማንስ ነው? ብለንም እንጠይቅ፤ |አንጋፋ ፖለቲከኛ´ የተባሉት አቶ ስዬ አብርሃ ማናቸው? የየትኛው ፓርቲ አባልና ከየትኛው ወገንስ ነበሩ? የሚሉ ጥንተ ነገሮችንም ጨምረን እንመርምር።

በአናቱም ካልተብራራ  ቃለ መጠይቅ መነሻ ተመስገን "ህዝቡ እያምሰለሰለ" እንደሆነ ግልፅ ይዘት ያለው ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ያስቻለው ምክንያት ምንድ ነው? ብለንም እንጠይቅ፤ መተንተኑ የኛ የጋዜጠኞች ድርሻ ነው የሚል ማስቀየሻ እና መዘላበድ አያስፈልግም። በአጭሩ ምላሹ ተመስገንና ስዬ አብርሃ በዜሮ ድምር ፖለቲካ መርህ አንድ አካል አንድ አምሳል የሆኑ ስለአመጽ የተፈጣጠሙ መሆናቸው ነው። ስለሆነም በዚህ ምላሽ መነሻነት ተመስገን "የመተንተን ስራ የእኛ የትንንሾቹ ካድሬዎች ነው።" ብሎ እርግጡን ቢነግረን የተሻለ ነበር።

የትኛው ህዝብ ብሎ የሚጠይቀው ተመስገን የአማራ የትግራይ የኦሮሞ ---እንደሆነ አቶ ስዬ ሊገልፁልን ይገባ ነበር ከማለቱ ብዙም ሳይርቅ በዛው ገጽ "ይሄ ህዝብ እኮ የሚታመን አይደለም። ታሪክ ሲሰራም ዛሬ ወይም ነገ ታሪክ እሰራለሁ ብሎ ቀጠሮ ሰጥቶ አይደለም። ከፈለገ ፈለገ ነው የሆነ ሆኖ ግን ስዬ እንዳሉት የሚንሰለሰል ነገር እንዳለ ግልፅ ነው።" ገጽ232 ይለናል።

አቶ ስዬ በጥቅሉ ህዝብ እያንሰለሰለ ነው ማለታቸውና የትኛውን ህዝብ እንደሆነ አለማብራራታቸው አንተን ግራ አጋብቶህ ከነበረ ለምን መልሰህ "ይሄ ህዝብ" ስትል የትኛው እንደሆነ ሳታብራራ አስቀመጥከው? ለነገሩ የትኛው እንደሆነ ግልጽ በመሆኑ ይመስለኛል የዘለልከው። "ከፈለገ ፈለገ ነው" የተባለው "ህዝብ" ሳይሆን እፍኝ የማትሞሉት አንተና መሰሎችህ ናችሁ።

‵እኔም አሸባሪ ነኝ′ ወደሚለው አጀንዳ ስንመጣ ብዙ ማብራራት የሚያስፈልገው አይመስለኝም። በ4ቱም ክፍል ያቀረብኳቸውን መጣጥፎችና በዚህኛውም ክፍል የተገለፁተን ቀዳሚ ነጥቦች መነሻ በማድረግ አዎ አንተም የጥፋተኝነት ውሳኔ እንደተላለፈባቸው አጋሮችህ ነኝ እያልከን ነወይ? ብዬ እጠይቅሃለሁ፡፡

ቀጥዬም ‵ቁሳርም ይደነግጣል?′ ወደሚለው ጭራና ቀንድ ወደሌለው መጣጥፍ አልፋለሁ። ይሄም ቢሆን ያው የተለመደውና ስለ ጨኸት ምህላ የተደረገበት፣ ማህሌተ ገንቦ የተወረደበት አጀንዳ ነው። ነገር ግን በዚህ አጀንዳ ላይ ለማብራሪያነትና ለጨኸት ማጠናከሪያነት የተመረጡት አስረጂዎች እራሱ ገርፎ እንደሚጮኸው ጅራፍ አይነት የተመስገን እና ዙሪያውን ማንነት የሚያጋልጡ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።

ተመስገን ቀደም ብለን በተመለከትነው እና "የተቃዋሚዎቹ ሰፈር እንደምን ከረመ?" በሚለው መጣጥፉ የመደራጀት እጥረት የተቃዋሚውን ሰፈር ጭር አድርጎታል፣ ስለሆነም ተደራጁ ፣መደራጀት የፖለቲካ ጀግንነት ነው። ሲል እንዳላነበረ በኢህአዴግ ጥላ ስር የሚደራጁ ፎረሞች የገገርው ፓርቲ መደናገጥ ምልክቶች ሆነው ቀርበዋል። በኢትዮጲያ ታሪክ እና ዕድሜ ልክ ህዝብ የተቆጨበትን ቀርቶ ሌላም እንኳ ቢሆን መገደብ በየትኛው መስፈሪያና መለኪያ ነው የመደንገጥ ምልክት የሚሆነው?። አባይን መገደብ የሃገሪቱ የልማት ደረጃን ፣የመንግስትን ቁርጠኝነትና አገልጋይነት የሚያረጋግጥ፣ መጪው ጊዜ ብሩህ እንደሆነ የሚያመላክት ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ የዜሮ ድምር ስብስቡን መንደር የሚያደናግጥና የሚያነቃንቅ እንጂ በቁሳር የተሰየመው መንግስት መደናገጥ ምልክት አይደለም።

ሌላም አላላችሁ ደግሞ ቀጥሎ የሚመጣ ‵ሞት የማይፈሩ ወጣቶች′ ይላል ርዕሱ ። የመጣጥፉ መነሻ ምክንያት ‵የቁጭትና የህዳሴ ትውልድ′ በሚል በአንድ ወቅት የቀረበው የኢቲቪ ዶክመንተሪ ፊልም ነው።

|የሆነ ሆኖ ብዙ "ሞት አይፈሬ" ወጣቶችን አይተናል። በተለይ በእኔ ትውልድ። በምርጫ 97 እና በድህረ ምርጫው ወጣትነት አብዮት እንደሆነ ያየንበት ወርቃማ ዘመን ነበር።´ ገጽ 248

|ወጣትነት አብዮት ነው። የቱኒዚያው ቦኢዚዝም ልክ እንዳንተ ወጣት ነበር። ያውም "ወጣት የነበር ጣት´ ገጽ 250

እኔ ደግሞ በምርጫ 97 እና ድህረ ምርጫ ያየነው ወጣትነት አብዮት ሳይሆን ስሜት ነው። ወጣትነት ለመምረጥ እድሜው ያልደረሰና ልክ እንደተመስገን የምርጫ ካርድ የሌለው በአንዳንድ ለአቋራጭ ሥልጣን በቋመጡ ኃይሎች ግፊት ተደናግሮ፣ ተታሎና በውኸምብር ውስጥ ገብቶ ሁኔታውን በውል ሳይረዳ በነበረበት አጋጣሚ የተወሰኑ ወጣቶች በስሜታዊነት ተውጠው አውቶቡስ ያቃጠሉበት ከገዛ ጥቅማቸው ጋር የተጋጩበት ወጣትነት ነው በምርጫ 97 ያየነው እልሃለሁ።

አሁን ግን ወጣትነት ተቀይሯል። "የነብር ጣት" ያልከው ወጣት ሰምቶህ ቢሆን ኖሮ ከቱኒዚያና ቦአዚዝም በቀደማችሁ ነበር። ሆኖም ወጣትነት አሁን ስራ ነው ። ወጣትነት ስለ ጥቅም መደራጀት ነው፣ ወጣትነት ከገዛ ጥቅም ጋር መዋደድና ዘብ መቆም ነው። ስለሆነም ትውልዱ የስሜት ሳይሆን |የቁጭትና የህዳሴ ትውልድ´ ሆኗል።

እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ምኞታችሁ ሁሉ ከንቱና የማይሳካ ነው። መንገዱ ጥርጊያ ነው ሜዳውም ሰፊ ነው፣ ገበያውም ነፃ ነው ለሁሉም እኩል እድል ተሰጥቷል። ተኝታችሁ ከምታልሙበት የቅዠት ዓለም ፈጥናችሁ ውጡ፣ ባይረፍድባችሁ ጥሩ ነው። የተሰጣችሁን እድል ተጠቀሙበት። በአንተ አባባልና ፍላጎት ከተቃኘው ከወጣት "የነብር ጣት" የአመጽ አመለካከትህ ጋር ተፋቱና ከቁጭትና ከህዳሴው ትውልድ ጋር ተጋቡ።